ትንሳኤ ኢትዮጵያ
Tinsae Ethiopia

# የግፍ አገዛዝ በቃ!

ከትንሳኤ ኢትዮጵያ የአርበኞች ህብረት

ላለፉት 20 ዓመታት መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸሙት ግፍ ተዘርዝሮ አያልቅም። በግንቦት ወር 1997 በተደረገው ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ የመለስን አገዛዝ በቃኝ ብሎ ነበር። ሆኖም ግን መለስ ዜናዊ የህዝብን ድምጽ አክብሮ ስልጣኑን ማስረከብ ሲገባው የንጹሃን ዜጎችን ደም በአደባባይ አፈሰሰ። በዙዎችን አሰረ፥ ደበደበ፥ ለስደት ዳረገ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የሚበሉት አጥተው በሚራቡባት ኢትዮጵያ መለስና ቤተሰቦቹ በሚዘርፉት የህዝብ ንብረት በአሜሪካና እና የአውሮፓ ከተሞች ዘመናዊ ቤቶች ያሰሩ ጀመር። ከአርሶ አደሩ መሬት እየቀሙ ለህንድ፥ ለቻይና እና ለሳውዲ ባለሃብቶች አከፋፈሉ። በብዙ ሺዎች የሚቀጠሩ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው መኖር አቅቷቸው እየተሰደዱ ናቸው። ሴቶች እህቶቻችን በሀገራቸው ስራ ሰርተው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መደገፍ ባለመቻላቸው በየአረብ አገር ተሰደው እየደረሰባቸው ያለውን መከራና ግፍ በየጊዜው እየሰማን እናዝናለን። ስንቱን ግፍ ዘርዝረን እንችለዋለን? ኢትዮጵያውያን ተረገጥን፥ ተሰቃየን፥ ተዋረድን፥ በቁም ሞት ሞትን። መቼ ነው በቃን የምንለው?

ጊዜው አሁን ነው። መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ 20ኛ ዓመት የስልጣን ዘመናቸውን በግንቦት ወር ለማክበር ሰፊ ዝግጅት ጀምረዋል። እየተራቡ ካሉ ህጻናት በተዘረፈ ገንዘብ ዊስኪና ሻምፓኝ ሊራጩ፥ ዳንኪራ ሊረግጡ እየተዘጋጁ ነው። እኛም ግንቦት 2003 መለስ ዜናዊን በቃ የምንልበት ወር እንዲሆን ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ዝግጅት መጀመራችንን እያሳወቅን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የክተት ጥሪ እናስተላልፋለን።

የስልጣን ዕድሜዬንው ለማራዘም ሲል መለስ ዜናዊ እንደሊቢያው ጋዳፊ ዜጎች ላይ ከባድ ጉዳት ከማድረስ ወደኋላ ስለማይል ሊያደርስ ከተዘጋጀው ጉዳት ለመከላከል ሁሉም ኢትዮጵያዊ በያለበት ቅድመ-ዝግጅት እንዲያደርግ እንጠቁማለን።

መለስ ዜናዊ እንደለመደው የሀይማኖትና የጎሳ ግጭት ሊቆሰቁስ ስለሚችል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በያለበት ነቅቶ እንዲጠባበቅ።

የጦር ሰራዊት አባላት ከኢትዮጵያን ህዝብ ጎን በመቆም መለስ ዜናዊንና ግብረአበሮቹን ለፍርድ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት እንድትተባበሩ እንጠይቃለን።

ተጨማሪ መግለጫዎችንና ህዝባዊ ጥሪዎችን በሚቀጥሉት ቀናት እናሰራጫለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ትንሳኤ ኢትዮጵያ የአርበኞች ህብረት
የካቲት 29 ቀን 2003

ለግንኙነት
ኢሜይል tinsae.ethiopia@gmail.com
www.tinsae.org